# የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት

# ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ

# DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA

# OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

፪ኛ ዓመት ቁጥር 24
አርባ ምንጭ ታህሳስ 5 ቀን ፪ሺ፲፮ዓ.ም

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No 24
Arba Minch December. 2023


| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| አዋጅ ቁጥር 27/፪ሺ፲፮ ዓ.ም<br>የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ--ገፅ | Proclamation No. 27/2023<br>Enviromental Pollution control Proclamation of the South Ethiopia Regional State---Page 1 |
| **<u>አዋጅ ቁጥር 27/፪ሺ፲፮ ዓ.ም</u>**<br><br>**<u>የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ</u>**<br><br>አካባቢን መጠበቅ በተለይም የሰውን ጤንነትና በጎ ሁኔታ እንደዚሁም የሕያዋንን ደህንነትና የተፈጥሮን ሥነ ውበት ማቆየት የሁሉም ዜጋ ተግባርና ኃላፊነት በመሆኑ፤ | **PROCLAMATION NO. 27/2016**<br><br>**PROCLAMATION OF ENVIRONMENTAL POLLUTION CONTROL OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE**<br><br>WHEREAS, the protection of the environment and the safeguarding of human health and well-being, as well as the maintaining of the biota and the aesthetic value of nature are the duty and responsibility of all citizens; |

| | |
|---|---|
| አንዳንድ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ጥረቶች ልማቱን የሚቀለብስ ጎጂ አካባቢያዊ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ በመሆናቸው፤ | WHEREAS, some social and economic development endeavors may inflict environmental harm that could make the endeavors adviorse; |
| ዜጎች በንፁህና ጤናማ አካባቢ የመኖር መብት በሕገ-መንግሥቱ የተደነገገ በመሆኑና በክልላችን ልማት እየተስፋፋ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚፈጠሩ ነገሮች አካባቢን በማይበክልና የሰውን ጤንነትና በጎ ሁኔታ ላይ ችግር በማይፈጥር መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ፣ እንዲከማቹና እንዲወገዱ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ በማስፈለጉ፤ | WHEREAS, given that citizens' right to a clean and healthy environment is enshrined in the constitution, and considering the environmental challenges arising from the expansion of development in our region, there is a need for a legal framework to ensure that activities, storage, and disposal of materials are carried out in a manner that does not pollute the environment or negatively affect people's health and well-being. |
| የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 3 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል። | WHEREAS, considering that the environmental challenges arising from the expansion of development in our region, there is a need for a legal framework to ensure that activities, storage, and disposal of materials are carried out in a manner that does not pollute the environment or negatively affect people's health and well-being, given that citizens' right to a clean and healthy environment is enshrined in the constitution;<br><br>NOW, THEREFORE, the authority issued by regional constitution pursuant to Sub Article (3) of this Article (54), Council of South Ethiopia Regional State issued this proclamation. |

| | |
|---|---|
| **ክፍል አንድ**<br>**ጠቅላላ ድንጋጌዎች** | **PART ONE**<br>**GENERAL PROVISIONS** |
| **1. አጭር ርዕስ** | **1. Short title** |
| ይህ አዋጅ “የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 27/፪ሺ፲፮ ዓ.ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ | This proclamation may be cited as "Environmental Pollution Control proclamation No. 27/2016". |
| **2. <u>ትርጓሜ</u>** | **2. Definitions** |
| የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡- | Unless the context is interpreted otherwise, in this proclamation:- |
| 1 “ክልል” ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ነው፡፡ | 1. Region" means South Ethiopia Region f. |
| 2 “ቢሮ” ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የደን አካባቢ ጥበቃና ልማት ቢሮ ነው፡፡ | 2. "Bureau" means Forest. Environment Protection and Development Bureau of South Ethiopia Regional State |
| 3 “የአካባቢ መሥሪያ ቤት” ማለት ለደን አካባቢ ጥበቃና ልማት ቢሮ በክልል፣ በዞን፣በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር ኃላፊነት የተሰጠዉ የመንግሥት አካል ነዉ ፡፡ | 3. "Environmental Office" a government organ of the Region, Zone, Wereda, and City Administration entrusted with responsibility for the Forest Environment Protection Bureau. |
| 4 “የተቆጣጣሪነት መታወቂያ” ማለት በቢሮው ለሚመደቡ ተቆጣጣሪዎች የሚሰጥ ለቁጥጥር ስራ ብቻ የሚያገለግል የመታወቂያ ካርድ | 4 "Inspector's ID" means identification card issued to inspectors assigned by the Bureau; it is to be used solely for inspection work. |

| | |
|---|---|
| ነው። | |
| 5 “ከባቢ” ማለት በመሬት በከባቢ አየር በአየር ሁኔታና በአየር ንብረት፣ በውሀ፣ በህያዋን በድምጽ በሽታ በጣዕም በማህበራዊ ጉዳዮች እና በሥነ ውበት ሳይወሰን በተፈጥሮአዊ ሁኔታቸው ወይም በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉና በያሉበት በታ እንዲሁም መጠናቸው ወይም ሁኔታቸው ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ህያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ መስተጋብሮቶቻቸው ድምር ነው። | 5 Environment" means the totality of all materials whether in their natural state or modified or changed by human; their external spaces and the interactions which affect their quality or quantity and the welfare of humans or other living beings, including but not restricted to, land atmosphere, whether and climate, water, living things, sound, odor, taste, social factors, and aesthetics; |
| 6 “ኬሚካል” ማለት ንጥረ ነገር ፣ ያልተቀላቀለም ይሁን የተቀላቀለ ውህድ፣ ተቀምሞ በሰው የተሠራ ወይም ከተፈጥሮ የተገኘ ቁስ አካል ነው። | 6 "Chemical" means a mineral whether by itself, or in a mixture or in a preparation, whether manufactured or obtained from nature; |
| 7 “ፍሳሽ” ማለት ተጣርቶ ወይም ሳይጣራ ፤ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ወደ አካባቢ የሚለቀቅ ቆሻሻ ውሃ ወይም ሌላ ፍሳሽ ቆሻሻ ነው። | 7 "Effluent" means waste water, gas or other waste fluid, treated or untreated, discharged directly or indirectly into the environment; |
| 8 “የአካባቢ ደረጃ” ማለት የአካባቢ ጥራት ወይም የብክለት መጠን መለኪያ መሥፈርት ነው። | 8 "Environmental standard" means a benchmark for measuring environmental quality or pollution levels. |
| 9 “የአካባቢ ተቆጣጣሪ ወይም ተቆጣጣሪዎች” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ መሰረት የሚሰየም አካል ነው። | 9 "Environmental Inspector or Inspectors" means the body designated under Article 11 of this Proclamation. |
| 10 “ፍርድ ቤት” ማለት በክልሉ በሕግ አግባብ | 10 "Court" means a first instance, higher, and |

| | |
|---|---|
| መሰረት የተቋቋመ የመጀመሪያ ደረጃ ፣ የከፍተኛና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፡፡ | supreme court established pursuant to the regional law. |
| 11 “አደገኛ ነገር” ማለት በሰው ጤና፣ በአካባቢና በአካባቢ ሀብቶች ላይ ጉዳት የሚያደርስ ጠጣር፣ ፈሳሽ፣ ጋዝ፣ ጨረር፣ ተክል፣ እንስሳ ወይም ረቂቅ ሕዋስ ነው፡፡ | 11 "Hazardous material” means any substance in solid, liquid or gaseous state, or any plant, animal or micro organism that is injurious to human health or the environment |
| 12. “አደገኛ ቆሻሻ” ማለት ተፈላጊነት የሌለው ሆኖ በአካባቢ ወይም በሰው ደህንነትና ጤና ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚታመን ማንኛውም ነገር ነው፡፡ | 12. "Hazardous Waste" means any unwanted material that is believed to be deleterious to human safety or health or the environment; |
| 13. “በካይ” ማለት ፈሳሽ ፤ ጠጣር ወይም ጋዝ የሆነ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፤ | 13. "Pollutant" means any substance whether liquid, solid, or gas which directly or indirectly: |
| ሀ) ያረፈበትን የአካባቢ ክፍል ጥራት በመለወጥ ጠቀሜታ የመስጠት አቅሙን የሚያጓድል ወይም | (a) alters the quality of any part of the receiving environment so as to effect its beneficial use adversely; or |
| ለ) በሰው ጤና ወይም በሌሎች ሕያዋን ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ሊያደርስ የሚችል መርዝን፣ ሽታ፣ ክርፋትን፣ ጨረርን፣ ድምጽን፣ ንዝረትን፣ ሙቀትን ወይም ሌላ ክስተትን የሚያመነጭ ማንኛውም ነገር ነው፡፡ | (b) produces toxic substances, diseases, objec- tionable odour, radioactivity, noise, vibration, heat, or any other phenomenon that is hazar- dous or potentially hazardous to human health or to other living things; |
| 14.“ብክለት” ማለት በዚህ አዋጅ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ሕግ የተደነገገን ማንኛውንም ግዴታ ፣ ማዕቀብ ወይም ገደብ ጥሶ የማንኛውንም የአካባቢ | 14. "Pollution" means any condition which is hazar- dous or potentially hazardous to human health, safety, or welfare or to living things created by altering any physical, radioactive, |

| | |
|---|---|
| ክፍል ቁሳዊ ፣ ጨረራዊ ፣ ሙቀታዊ፣ ንጥረነገራዊ ፣ ሥነ-ሕይወታዊ ወይም ሌላ ባህሪይን በመለወጥ የተፈጠረ በሰው ጤና ወይም በጎነት ወይም ደግሞ በሌሎች ሕያዋን ላይ አደገኛ የሆነ ወይም አደገኛ ሊሆን የሚችል ሁኔታ ነው፡፡ | thermal, chemical, biological or other property of any part of the environment in contravention of any condition, limitation or restriction made under this Proclamation or under any other relevant law; |
| 15.“የድምጽ ብክለት” ማለት በሰው ጤንነትና ኑሮ ሁኔታ ላይ ጉልህ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ከኢንዱስትሪዎች፣ ከድርጅቶችና ከተለያየ የሰዎች ተግባራት የሚፈጠር ድምጽ ነው፡፡ | 15. “Noise pollution” means a noise emanating from industries, organizations, and various human activities that likelya cause a significant harm to human health and well-being. |
| 16.“መልቀቅ” ማለት በውል ታስቦም ይሁን ሳይታሰብ በካይን ወደ ማንኛውም የአካባቢ ክፍል መጨመር ነው፡፡ | 16. "Release" means placing any pollution in the environment in any way be it intentionally or otherwise. |
| 17.“ውሃ” ማለት የገፀ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ማለት ነው፡፡ | 17. "Water" means surface and ground water. |
| 18.“የውሃ አካላት” ማለት ወንዞች ፣ ሀይቆች ፣ ኩሬዎች ፣ ረግረጋማ ሬቶችና ምንጮች ናቸው፡፡ | 18. "Water bodies" means rivers, lakes, ponds, swamps, and springs. |
| 19.“አየር” ማለት በዙሪያችን በተፈጥሮ የሚገኝ የጋዞች ቅልቅል ነው፡፡ | 19. "Air" means the naturally occurring mixture of gases surrounding us. |
| 20 “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡ | 20 "Person" means any natural or juridical person. |
| **3. የፆታ አገላለጽ** | **3. Gender** expression |
| በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው | In this proclamation, what is expressed in the |

| | |
|---|---|
| የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡ | maceulain is also includes the femanen. |
| 4. የተፈጻሚነት ወሰን | **4.** Scope |
| ይህ አዋጅ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ውስጥ በሚገኙ ማንኛውም መንግሥታዊ ተቋማት ፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ፣ የንግድ ተቋማት ወይም ሰዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡ | This proclamation shall come into applicable on any public institutions or private organizations; on business sectors and persons found within the region of South Ethiopia. |
| **<u>ክፍል ሁለት</u>** | **PART TWO** |
| **<u>ስለ አካባቢ ብክለት አስተዳደርና ቁጥጥር</u>** | **Management and Control of Environmental Pollution** |
| 5. የብክለት ቁጥጥር | 5. Control of Pollution |
| 1 ማንኛውም ሰው ተገቢዉን የአካባቢ ደረጃ በመተላለፍ አካባቢን ሊበክል ወይም በሌላ ሰው በኩል እንዲበከል ሊያደርግ አይችልም፡፡ | 1. No person shall pollute or cause any other person to pollute the environment by violating the relevant environmental standard. |
| 2 የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ማንኛውንም በካይ ወደ አካባቢ በሚለቅ ሰው ላይ ቢሮው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም ሕጋዊ ዕርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡ | 2 The bureau may take an administrative or legal measure against a person who, in violation of law, releases any pollutant to the environment. |
| 3 በቢሮው ወይም በሚመለከተው የደን አካባቢ ጥበቃና ልማት መስሪያ ቤት ትዕዛዝ መሰረት ብክለትን ወይም ሌላ አካባቢያዊ ጉዳትን ሊያስከትል በሚችል የተግባር መስክ የተሰማራ ማንኛውም ሰው የቆሻሻ ማመንጨትን ለማስወገድ | 3 Any person engaged in any field of activity which is likely to cause pollution or any other environmental hazard pursuant to bureau or relevant Forest Environment Protection Development Bureau, shall install a sound technology that avoids or reduces, to the |

| | |
|---|---|
| ወይም ወደ ተፈለገው መጠን ለመቀነስ የሚያስችል ተገቢዉ ቴክኖሎጂና ቆሻሻን መልሶ በጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ዘዴዎች የመጠቀም ግዴታ አለበት፡፡ | required minimum, the generation of waste and, when feasible, apply methods for the recycling of waste. |
| 4 ብክለትን ያደረሰ ማንኛውም ሰው ቢሮው ወይም የሚመለከተው የደን አካባቢ ጥበቃና ልማት መስሪያ ቤት በሚወስነው ሁኔታና የጊዜ ገደብ መሰረት አካባቢውን ከበካይ ማፅዳት ወይም ለማፅዳት የወጣውን ወጪ የመሸፈን ግዴታ አለበት፡፡ | 4. Any person who causes any pollution shall be required to clean up or pay the cost of cleaning up the polluted environment in such a manner and within such a period as shall be determined by the bureau or by the relevant Forest .Environmental Protection and Development Office. |
| 5 በጤና ወይም በአካባቢ ላይ አደጋ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ በሚያሰጋ የሥራ እንቅስቃሴ ሊመጣ የሚችል ጉዳትን ለመከላከል ቢሮውና የታችኛው አካል በድርጅቱ ላይ የማሻሻያ ስልቶችን እንዲጠቀም ማድረግ፣ ወደ ሌላ በታ ማዛወር ወይም እስከ መዝጋት የሚደርስ ማንኛውንም አስፈላጊ እርምጃ መውሰድ ይችላል፡፡ | 5. When any work activity deemed to pose a risk to human health or to the environment, the bureau and lower bodies shall implement corrective actions; take any necessary measure upto the closure or relocation of organization in order to prevent harm. |
| 6. **ስለአደገኛ ቆሻሻ ፣ ኬሚካልና ጨረራ አመንጪ ቁስ አያያዝ** | 6. **Management of Hazardous Waste, Chemical and Radioactive Substance** |
| 1. ከቢሮው ፈቃድ ሳይዝ ማንኛውንም አደገኛ ቆሻሻን ማመንጨት ፣ ማስቀመጥ ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ ፣ ማምከን ፣ መጠቀም ወይም ማስወገድ የተከለከለ ነው፡፡ | 1. The generation, keeping, storage, transportation, treatment or disposal of any hazardous waste without a permiion from the bureau is prohibited. |

| | |
|---|---|
| 2. አደገኛ ቆሻሻ በመሰብሰብና በማስወገድ ሥራ የተሰማራ ማንኛውም ሰው በአካባቢ፣ በሰው ጤና ወይም በጎ ሁኔታ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለበት። | 2. Any person engaged in the collection and disposal of any hazardous waste shall take appropriate precaution to prevent any direct or indirect damage to the environment or to human health or well-being. |
| 3. ጨረር አመንጪ ቁስን ወደ ክልሉ ውስጥ ለማስገባት ፣ ከከርሰ ምድር ለማውጣት ፣ ለማጣራት ፣ ለማስቀመጥ እንዲሁም በክልሉ ውስጥ ለማሰራጨት ፣ ለማከማቸት ፣ ለማጓጓዝ ፣ በጥቅም ላይ ለማዋል ወይም ለማስወገድ የሚፈልግ ማንኛዉም ሰው በቅድሚያ ከቢሮው ፈቃድ ማግኘት አለበት። | 3. Anyone who wants to import, mine, process, keep, and to distribute within the region, store, transport, use or dispose radioactive substances to the region shall be subject to a permit from the bureau . |
| 4. አደገኛ ተብሎ የተመደበን ወይም ለተወሰነ አገልግሎት ብቻ እንዲውል የተወሰነ ኬሚካልን ወደ ክልሉ ውስጥ ለማስገባት ፣ ለመጠቀም ፣ ለማስቀመጥ፣ ለማሰራጨት ፣ ለማከማቸት ፣ ለማጓጓዝ ወይም ጥቅም ላይ ለማዋል ማንኛዉም ሰው ከቢሮው ፈቃድ ማግኘት አለበት። | 4. The importation, preparation, keeping, distribution, storage, transportation or use of a chemical categorized as hazardous or of restricted use, shall be subject to permition from the bureau. |
| 5. አደገኛ የሆነ ወይም ለተወሰነ አገልግሎት የሚውል ኬሚካልን በመጠቀም ፣ በማምረት ወይም በማጓጓዝ ወይም ኬሚካሉን በመነገድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ኬሚካሉ በተገቢዉ ደረጃ መሰረት መመዝገቡን፣ መታሸጉንና አስፈላጊው ምልክት የተለጠፈበት | 5. Any person engaged in the preparation, production, manufacturing or transportation or in trading in any hazardous or restricted chemical may ensure that the chemical is registered, packed and labeled as per the applicable standards. |

| | |
|---|---|
| መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡ | |
| 6. የአገልግሎት ጊዚያቸው ያለፉና የተበላሹ ኬሚካሎችና የተለያዩ ቁሶች በአግባቡ የመያዝና የማስወገድ ኃላፊነት የአምጭው ሲሆን ለማስወገድ ከቢሮው ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። | 6. The responsibility for the proper handling and disposal of expired and damaged chemicals and materials rests with the supplier, shall be subject to permition from the bureau for the disposal. |
| 7. ስለደረቅ ቆሻሻ አያያዝ | 7. Solid Waste Management |
| 1. ቢሮው ከሚመለከታቸው የክልል ተቋማት ወይም በቆሻሻ አያያዝ ኃላፊነት ከተሰጣቸው ክፍሎች ጋር በመተባበር የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ስርዓትን በማውጣት የደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ መሰብሰቡን፣ መጓጓዙን፣ እንደተገቢነቱም በጥቅም ላይ መዋሉን፣ መምከኑን ወይም ጉዳት እንዳያመጣ ተደርጎ መወገዱን ማረጋገጥ አለበት፡፡ | 1. In collaboration with the relevant regional institutions or the departments issued responsibility for waste management, the Bureau shall set a solid waste management system to ensure the proper collection of solid waste, transportation, proper utilization, management or disposal that prevents harm or damage. |
| 2. ቢሮው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓቶችን ብቃት መመዘንና የአተገበበራቸውንም ውጤታማነት መገምገም ፣ መከታተልና ማረጋገጥ አለበት፡፡ | 2. In collaboration with the concerned bodies, the bureau shall monitor and evaluate the adequacy of waste management and treatment systems, and ensure the effectiveness of their implementation. |
| 3. ለሕዝብ ክፍት የሆነ ቦታን የሚያስተዳድር አካል ፣ ምንጊዜም በቂና ተስማሚ የመጸዳጃ ቤት ፣ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎችና አስፈላጊ የሆኑ መገልገያዎች በቦታው መኖራቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡ | 3. Any person responsible for the maintenance of any premise to which the public has access shall, at all times, ensure that adequate and suitable toilets and containers and other required facilities are provided for the disposal |

| | |
|---|---|
| | of waste. |
| 4. ቢሮው አግባብነት ካላቸው ሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር የደረቅ የቆሻሻ ማስወገጃ መገልገያዎችን መገምገምና በበቂ ሁኔታ መሟላታቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡ | 4. The bureau shall, in collaboration with the other relevant institutions, monitor the situation with regard to the availability of waste disposal facilities and take the necessary measures to ensure that their availability is satisfactory. |
| 5. የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ሥፍራ ከመገንባቱ አስቀድሞ የሚያስገነባው አካል የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ለቢሮው አቅርቦ ይሁንታ ማግኘት አለበት፡፡ | 5. Before building a solid waste disposal site, the entity that will build it must submit an environmental impact assessment document to the office and get approval. |
| 6. አደገኛ የሆኑ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ አደገኛ ካልሆኑት መለየት አለበት፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡ | 6. The handling and disposal of hazardous waste must be separated from non-hazardous waste. The detilles shall be determined by regulation. |
| 8. ስለውሃ አካላት አጠባበቅና አጠቃቀም | 8. Maintenance and treatment of water bodies |
| 1. ማንኛውም ሰው በውሃ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ብክለትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ተግባራትን ማከናወን የተከለከለ ነው፡፡ | 1. Anyone is prohibited from undertaking activity, directly or indirectly, that likely cause pollution to the water. |
| 2. በውሃ አካላት ውስጥ ወይም ውሃን መበከል በሚችል ርቀት ላይ የተሸከርካሪ እጥበትና ማንኛውንም የግንባታ፣ የግብርናና ሌሎች ተግባራትን ማከናወን የተከለከለ ነው፡፡ ከወንዙ የሚኖረውን ሌሎች የሚያስከለክሉ ተግባራት | 2. Washing vehicles and carrying out any construction, agricultural, or other activities in or within a distance that could pollute water bodies is prohibited. Other activities that prohibit access to the river will be listed in guidelines issued by the Bureau. |

| | |
|---|---|
| ቢሮው በሚወጣው መመሪያ ይዘረዘራል። | |
| 3. የውሃ አካላትን ለመስኖ ፣ ለኢንዱስትሪዎችና ለሌሎች አገልግሎት ለማዋል የሚፈልግ ሰው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ ለቢሮው አቅርቦ ይሁንታ ሳይሰጠው መጠቀም የተከለከለ ነዉ። | 3. A person who wants to use water bodies for irrigation, industrial purposes, or other services shall submit an environmental impact assessment tool to the Bureau and obtain authorization before use. |
| 4. በክልሉ በሚገኙ የውሃ አካላት ዙሪያ የሚደረግ ማንኛውም ግንባታ ወይም የልማት ሥራዎች በውሃ አካላት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማድረስ የለበትም። በውሃ አካላት ዙሪያ የሚደረጉ ግንባታዎች ርቀት መጠን ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል። | 4. Any construction or development activities carried out around water bodies in the region shall not cause negative effect to the water bodies. The minimum distance for construction around water bodies will be determined by guidelines issued by the Bureau. |
| 9. ስለድምጽ ብክለት | 9. Noise pollution |
| 1. በክልሉ የሚገነቡና የሚቋቋሙ ልማቶች ፣ ንግድ ቤቶች፣ እንዱስትሪዎች ፣ የዕምነት ተቋማት ፣ ማህበራዊ አገልግሎት መስጫዎችና ሌሎች ግንባታዎች ሁሉ የድምጽ ብክለት ሊያስወግዱ በሚችሉበት አግባብበ ጥናት ላይ ተመስርተው መገንባት ይኖርባቸዋል። | 1. All developments, businesses firms, industries, religious institutions, social service providers, and other constructions built in the region shall be constructed based on the study that minimizes noise pollution. |
| 2. ቢሮው ለወደፊቱ የሚደረጉ ግንባታዎች እንደየ ዘርፋቸው ተቋማዊ ባህሪያቸውን ባገናዘበ ሁኔታ በተከለሉ የኢንዱስትሪ ዞኖች ፣ የንግድ ፣ የመኖሪያ ፣ የትምህርትና የጤና ተቋማት አካባቢዎች ተለይተው የድምጽ ብክለትን ቁጥጥር ሊያሳካ በሚችል መልኩ እንዲገነቡ ማድረግ ይኖርበታል። | 2. The Bureau shall ensure that future constructions are built in designated industrial zones, commercial, residential, education, and health institutional areas, in line with their respective sectors and taking into account institutional characteristics, in a manner that enables effective noise pollution control. |

| | |
|---|---|
| 3. ማንኛውም ሰው በመኖሪያ ቤቱ ፣ በንግድ ተቋሙ ፣ በማምረቻ ቦታው ፣ በእለታዊ እንቅስቃሴው ሁሉ የማይፈለግና ከመጠን በላይ ድምጽን ከማመንጨት መቆጠብ ይኖርበታል፡፡ | 3. Every person shall refrain from generating undesirable and excessive noise in their residences, businesses, production place, and every day activities. |
| 4. በሰው ልጆች ጤንነት ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ የድምጽ አመንጪዎች የድምጽ ብክለትን ለመቀነስ የሚረዱ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡ | 4. Necessary measure shall be taken to minimize noise pollution of noise generators that casue harm to human health. |
| 5. ሥፍራንና ጊዜን ባላገናዘበ መልኩ አካባቢና ሰውን የሚረብሹ ድምጾችን በሚያመነጩ አካላት ላይ ቢሮው ተመጣጣኝ እርምጃዎችን መውሰድ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡ | 5. The Bureau may take propetional measures against individuals generating disruptive noises at inappropriate times and places that disturb the environment and people. The detilles shall be determined by the Regulation. |
| 10. ስለ አካባቢ ደረጃዎች | 10. Environmental standards |
| 1. በፌዴራል አካባቢና አየር ንብረት ለውጥ ባለስልጣን የወጣ የአካባቢ ደረጃ በክልሉ ተግባራዊ ይደረጋል ፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቢሮው ተግባራዊ መሆን የሚችሉ የክልሉን የአካባቢ ደረጃዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ማዘጋጀት ይችላል፡፡ | 1. Environmental standards issued by the Federal Environment and Climate Change Authority shall be implemented in the region. However, the bureau may formulate and implement its own regional environmental standards on various issues when it is neccessary. |
| 2. በሰው ጤናና በአካባቢ ላይ የሚያስከትለውን ጠንቅ ለመግታት ቢሮው በሚከረፋ ሽታ ምንጮች ላይ ቁጥጥር ማካሄድ አለበት፡፡ | 2. Sources of noxious odour shall be regulated by the bureau; so that the nuisance they cause to person’s health and environment is prevented. |

| | |
|---|---|
| 3. የሕዝብ ጥቅምን ለማጎልበት ሲባል አግባብ ያለውን ደረጃ እንዲያሟሉ የሚጠበቅባቸውን የተወሰኑ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ተፈጻሚነት ቢሮው ለተወሰነ ጊዜ እንዲታለፍ ሊፈቅድ ይችላል። የጊዜው መጠን ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል። | 3. The Bureau may, for a fixed period of time, authorize the waiver of the duty to comply with some requirements of specified environmental standards in order to promote public benefit; the directive issued by the bureau will determine the time period. |
| ክፍል ሶስት | Part three |
| ስለአካባቢ ተቆጣጣሪዎች፣ ስለይግባኝና ቅጣት | Environmental inspectors, appeals, and penalties |
| 11. ስለአካባቢ ተቆጣጣሪዎች | 11. Environmental inspectors |
| 1. የአካባቢ ተቆጣጣሪዎች ከዚህ በኃላ “ተቆጣጣሪዎች” እየተባሉ የሚጠሩ በቢሮው ወይም አግባብ ባለው አካል ይሰየማሉ። | 1. Environmental inspectors (hereinafter referred to as "inspectors") shall be assigned by the bureau or by the relevant concerned body. |
| 2. ተቆጣጣሪዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ መሰረት ሥልጣንና ተግባራቸውን ሲወጡ ሥራቸውን በትጋትና ያለአድልዎ የመፈጸም ግዴታ አለባቸው። | 2. Inspectors shall exercise due diligence and impartiality in the discharge of their powers and functions under Article 12 of this Proclamation |
| 3. ተቆጣጣሪዎቹ ለሥራ የሚያስፈልጋቸውን የደህንነት አልባሳትና አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ቢሮው ማሟላት ይኖርበታል። ስለተቆጣጣሪነት መታወቂያ ይዘትና ስለተቆጣጣሪዎች ሥነ-ምግባር ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይዘረዘራል። | 3. The bureau shall provide the inspectors with the necessary safety attire and essential equipment required for the work. The scope of inspection identification and the code of conduct for inspectors will be specified in guidelines issued by the bureau. |
| 12. ስለተቆጣጣሪዎች ሥልጣንና ተግባር | 12. Powers and duties of inspectors |

| | |
|---|---|
| 1. የአካባቢ ተቆጣጣሪዎች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል | 1. Environmental inspectors shall have the following powers and functions |
| ሀ/ የአካባቢ ደረጃዎችና ተዛማጅ ግዴታዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፤ | A/ ensure compliance with environmental standards and related requirements; |
| ለ/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ እና ፮ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ሳያሳዉቁ ወይም ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳይዙ በማንኛዉም ተገቢ መስሎ በሚታያቸዉ ጊዜ ወደ ማንኛዉም ቦታ ወይም ቅጥር ግቢ መግባት፤ | b/ without prejudice to Sub-Articles (3) and (6) of this Article, enter any land or premises at any time which seems appropriate to them without prior notice or court order; |
| ሐ/ ማንኛውንም ሰው ብቻውን ወይም በምስክር ፊት መጠየቅ፤ | C/ question any person alone or in the presence of witnesses; |
| መ/ ከብክለት ጋር ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ወረቀት ፣ ማህደር ወይም ሌላ ሰነድ መፈተሽ ፣ መገልበጥ ወይም ለይቶ መቅዳት፤ | d/ check, copy or extract any paper, file or any other document related to pollution; |
| ሠ/ የማንኛውንም ቁስ ናሙናዎች እንደ አስፈላጊነቱ ያለክፍያ መውሰድና በአካባቢ ወይም በሕይወት ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን መመርመር ወይም ማስመርመር፤ | e/ take free of charge samples of any material as required and carry out or cause to be carried out tests to determine whether or not it causes harm to the environment or to life; |
| ረ/ ይህ አዋጅ እና አግባብ ያለው ማንም ሌላ ሕግ መከበሩን ለማረጋገጥ ሸቀጥን ፣ የአመራረት ሂደትን ወይም መገልገያን በፎቶግራፍ ማንሳት ፣ መለካት ፣ | f/ take photographs, measure, draw, or examine any commodity, process or facility in order to ensure compliance with this Proclamation and with any other relevant law; |

| | |
|---|---|
| መሳል ወይም መፈተሽ፤ | |
| ሰ/ ይህን አዋጅ ወይም አግባብ ያለውን ሌላ ሕግ በመተላለፍ ጥፋት ተፈጽሞበታል የተባለ መሳሪያን ወይም ሌላ ነገርን መያዝ፤ | G/ seize any equipment or any other object which is believed to have been used in the commission of an offence under this Proclamation or any other relevant; |
| 2. የተመደበው ተቆጣጣሪ  የዚህን አዋጅ ወይም ማንኛውንም አግባብ ያለውን ሕግ ድንጋጌ ለተላለፈ ሰው የመተላለፉን ምክንያት ይዘረዝርለታል ፤ ይህንኑ መተላለፍ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለማስቀረት መወሰድ ያለበትን እርምጃ በመግለፅም እርምጃው እንዲወሰድ ሊያዝ ይችላል፡፡ | 2. When a person contravenes any of the provisions of this Proclamation or of any other relevant law, the inspector on duty shall specify the matter constituting the contravention and may also specify the measures that shall be taken to remedy the contravention within a given period of time. |
| 3. የተመደበው ተቆጣጣሪ ማንኛውንም እንቅስቃሴ በአካባቢ ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል ብሎ ሲጠረጥር እንቅስቃሴውን እስከ ማስቆም የሚደርስ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ | 3. When an inspector on duty suspects that any activity may cause damage to the environment, he shall order the taking of corrective measures upto the immediate cessation of the activity. |
| 4. ማንኛውም የተመደበ ተቆጣጣሪ በቢሮው ወይም አግባብ ባለው አካል የተሰጠ የመሥሪያ ቤቱ ማህተም ያለበት መታወቂያ መያዝ ፤ ሲጠየቅም ማሳየት አለበት፡፡ | 4. Every inspector shall have an identity card issued by the Bureau or by the relevant concerned, bearing its official seal and show it when requested; |
| 5. ናሙና ሲወሰድ ባለንብረቱ የመገኘት ወይም ወኪል የመላክ መብት ስላለው ይህንኑ መብት እንዲያውቀው መደረግ አለበት፡፡ | 5. Whenever a sample is to be taken, the proprietor has the right to be present or to send his representative and he shall be informed accordingly. |
| 6. የሥራ አፈጻጸም ቅልጥፍናውን የሚበድልበት | 6. When an inspector on duty visits an undertaking, he shall notify the proprietor |

| | |
|---|---|
| ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የተመደበ ተቆጣጣሪ ወደ ማንኛዉም ድርጅት ቅጥር ግቢ ወይም በታ ሲገባ ለባለንብረቱ ማስታወቅ አለበት፡፡ | unless he considers that such notification may be prejudicial to the efficient performance of his duty. |
| 13. ስለይግባኝ | 13. Right to appeal |
| 1. ተቆጣጣሪው በወሰደው ማንኛውም እርምጃ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው፤ እርምጃው ከተወሰደበት ቀን አንስቶ እስከ 30 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ለቢሮው የበላይ ኃላፊ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ | 1. Any person dissatisfied with any of the measures taken by the inspector may submit grievance to the Head of the bureau within thirteen days from the date on which the measure was taken. |
| 2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ መሰረት ቅሬታ የቀረበለት የስራ ሃላፊ ቅሬታው በቀረበ በ ፲ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡ | 2. The officer in charge who receives a grievance as provided under Sub-Article 1 of this article shall give a decision within 10 days of the grievance being submitted. |
| 3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ መሰረት ውሳኔ ያልተሰጠ በመሆኑ ወይም የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ባለመሆኑ ቅር የተሰኘ ሰው ውሣኔው ከተሰጠበት ወይም የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ ካለፈበት ቀን አንስቶ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡ | 3. Any person dissatisfied because no decision has been given as provided under Sub-Article (1) and (2) of this Article, or feels that the decision given is inappropriate, may appeal to the authorized court within thirty days from the date on which the decision was given or the deadline for decision has elapsed. |
| 14. ስለ መክሰስ መብት | 14. Right to Standing |
| 1. ጉዳዩ የሚመለከተው መሆኑን ማስረዳት ሳይጠበቅበት ማንኛውም ሰው በአካባቢ ላይ ጉዳት አድርሷል ወይም ጉዳት ሊያስከተል የሚችል ተግባር እየፈጸመ ነው በሚል በማንኛውም ሰው ላይ | 1. Any person shall have, without the need to show any vested interest, the right to lodge a complaint at the bureau against any peron allegedly causing actual or potential damage to the environment. |

| | |
|---|---|
| ለቢሮው ቅሬታ የማቅረብ መብት አለው። | |
| 2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ መሰረት ቅሬታ የቀረበለት ቢሮው ወይም የአካባቢ መሥሪያ ቤት ቅሬታው በቀረበ በ፴ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት። | 2. The bureau that receives a grievance pursuant to Sub-Article 1 of this article shall give a decision within 30 days of the grievance being submitted. |
| 3. ቢሮው ቅሬታው በቀረበ በ፴ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በውሳኔ ካልተስማማ ውሳኔ ከተሰጠበት የጊዜ ገደብ ካለፈበት ቀን አንስቶ በ፴ ቀናት ውስጥ በፍርድ ቤት ክስ መመሥረት ይችላል። | 3. When the bureau fails to give a decision within thirty days or when the person who has lodged the complaint is dissatisfied with the decision, he may institute a court case with in thirty days from the date the decision was given or the deadline for decision has elapsed. |
| ፲፭. ስለጥፋትና ቅጣት | 15. Offences and Penalties |
| 1. ይህን አዋጅ ወይም አግባብ ያለውን ሌላ ሕግ የተላለፈ ፤ ነገር ግን ጥፋቱ በወንጀል ሕግም ሆነ በዚህ አዋጅ ቅጣት ያልተመደበለት ሆኖ የተገኘ ማንም ሰው ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ፤ | 1. A person who, under this Proclamation or under any other relevant law, commits an offence for which no penalty is provided for either in the Penal Code or under this Proclamation, is liable on conviction; |
| ሀ/ የተፈጥሮ ሰው ሲሆን ከመቶ ሺ ብር በማያንስና ከሁለት መቶ ሺ ብር በማይመልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአምስት አመት በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል። | A/ in the case of a natural person, to a fine of not less than one hundred thousand Birr and not more than two hundred thousand Birr or an imprisonment of not more than five year or both; |
| ለ/ በሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው ሲሆን ከሁለት መቶ ሺ ብር በማያንስና ከአራት መቶ ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል። | B/ in the case of a juridical person, to a fine of not less than two hundred thousand Birr and not more than four hundred thousand Birr. |

| | |
|---|---|
| 2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /፩/ መሰረት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ የተፈፀመውን ጥፋት ማወቅ የነበረበትና ኃላፊነቱን በብቃት ያልተወጣው የሥራ ኃላፊዉም ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአስር ዓመት በማይበልጥ እስራትና ከሁለት መቶ ሺ ብር በማያንስና ከሦስት መቶ ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮና ወይም በሁለቱም ይቀጣል። | 2. Where a juridical person is convicted pursuant to Sub-Article (1) of this Article, the officer in charge who should have known the commission of the offence, and who failed to fulfill his duty appropriately shall be liable to an imprisonment of not less than five years and not more than ten years, and a fine of not less than two hundred thousand Birr and not more than three hundred thousand Birr or both. |
| 3. በወንጀል ሕግ መሠረት የከበደ ቅጣት የማያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ቅጣቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ። | 3. Unless the provisions of the Penal Code provide more severe penalties, the penalties laid down under this Proclamation shall be applicable. |
| ፲፮. ከተቆጣጣሪዎች ጋር በተያያዘ ስለሚፈጸሙ ጥፋቶች | 16. Offences related to Inspectors |
| 1. የተመደበ ተቆጣጣሪን ሥራውን እንዳያከናውን ያደናቀፈ ወይም ያሰናከለ ወይም በሀሰት የከሰሰ ተቆጣጣሪው በሕግ መሠረት የጠየቀውን ወይም ያዘዘውን ያልፈጸመ ፣ በማስመሰል ተቆጣጣሪ ነው ሊባል የሞከረ ፣ ተቆጣጣሪው ወደ ማንኛውም ቦታ ወይም ቅጥር ግቢ እንዳይገባ ወይም መዛግብት እንዳይመረምር ያደናቀፈ ፣ ማንኛውንም ወረቀት ፣ ማህደር ወይም ሌላ ሰነድ እንዳይፈትሽ ፣ እንዳይገለብጥ ወይም ለይቶ እንዳይቀዳና መረጃ የከለከለ ፣ የተሳሳተ መረጃ የሰጠ ማንም ሰው በዚህ | 1. A person commits an offence if he hinders or obstructs an inspector on duty in the execution of his duty, fails to comply with a lawful order or requirement made by an inspector, impersonates an inspector, or refuses an inspector entry into any land or premise or hinders an inspector from getting access to records, prevents an inspector from checking, copying or extracting any paper, file or any other document, withholds, misleads or gives wrong information to an inspector. |

| | |
|---|---|
| አዋጅ መሰረት ጥፋተኛ ይሆናል፡፡ | |
| 2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ /፩/ መሰረት ጥፋት የፈጸመዉ፡- | 2. The one who commits an offence pursuant to Sub Article (1) of this Article:- |
| ሀ/ የተፈጥሮ ሰው ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ ከመቶ ሺ ብር በማያንስ ከሁለት መቶ ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤ | A/ a natural person who commits an offence is liable, on conviction, to a fine of not less than one hundred thousand Birr and not more than two hundred thousand Birr; |
| ለ/ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ደግሞ ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ ከብር መቶ ሃምሳ ሺ በማያንስና ከብር ሁለትመቶ ሃምሳ ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል ፤ የሥራው ኃላፊውም ከአምስት አመት በማያንስ እና ከአሰር ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም ከመቶ ሃምሳ ሺ ብር በማያንስና ከሁለት መቶ ሃምሳ ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡ | B/ in the case of a juridical person offence is liable, on conviction, to a fine of not less than one hundred fifty thousand Birr and and not more than two hundred fifty thousand Birr, and imprisonment of the officer in charge for a term of not less than five years and not more than ten years or a fine of not less than one hundred fifty thousand Birr and not more than two hundred fifty thousand Birr or both. |
| 17. መዛግብትን በተመለከተ ስለሚፈፀሙ ጥፋቶች | 17. Offences relating to records |
| ማንኛዉም ሰው በዚህ አዋጅ ወይም አዋጁን ተከትሎ በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሰረት በመዝገብ እንዲያሰፈር የተጠየቀውን የእንቅስቃሴ ፣ የምርት ፣ የቆሻሻ ዓይነት ባሕሪይ ፣ መጠን ወይም ሌላ ተፈላጊ መረጃ በተገቢው ሳይመዘግብ ከቀረ ወይም በመዝገብ የሰፈረውን ከለወጠ፣ ከሃምሳ ሺ ብር በማያንስና መቶ ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡ | Any person commits an offence if he/she fails to comply with this Proclamation or any regulation and directive issued following this Proclamation to keep records of activities, products, the types, amount, characteristics of waste, or of any other information appropriately; or if he/she alters any record shall be liable to a fine of not less than fifty thousand Birr and not more than one hundred |

| | |
|---|---|
| | thousand Birr. |
| 18. አደገኛ የሆነ ቆሻሻንና ሌላ ቁስን በተመለከተ ስለሚፈፀም ጥፋት | 18. Offences relating to waste and other material that is hazardous |
| 1. ማንኛዉም ሰው አደገኛ ቆሻሻን ወይም አደገኛ ነገርን አግባብ ባላቸው ሕጎች መሰረት ካልያዘ ፣ መለጠፍ ያለበት ዝርዝር አሳስቶ ከለጠፈ ወይም ጭራሹን ካልለጠፈ ፣ መረጃን ከነፈገ ፣ ያልተፈቀደ የአደገኛ ቆሻሻ ዝውውርን ለማካሄድ ከሞከረ ፣ ያካሄደ ፣ እንዲካሄድ ለመርዳት የሞከረ ወይም ከረዳ ፣ አደገኛ ቆሻሻን አግባብነት በለሌው ቦታ ከጣለ ወይም ከለቀቀ በዚህ አዋጅ መሰረት ጥፋተኛ ይሆናል። | 1. As provided under this Proclamtion, any person commits an offence if he/she fails to manage a hazardous waste or another substance according to the relevant laws, mislabels or fails to label or in any way withholds information about any hazardous waste or other material or attempts to take part or takes part or attempts to aid or aids in the illegal traffic of any hazardous waste or other material or improperly disposes of or releases hazardous waste. |
| 2. በዚህ አንቀጽ ንዕስ አንቀጽ/፩/ መሰረት ጥፋት የፈፀመ የተፈጥሮ ሰው ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ ከመቶ ሺ ብር በማያንስና ከመቶ ሃምሳ ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል። | 2. A natural person who commits an offence under Sub Article (1) of this Article is liable, on conviction, to a fine of not less than one hundred thousand Birr and not more than one hundred fifty thousand Birr. |
| 3. ጥፋቱን የፈፀመዉ በህግ የሰዉነት መብት የተሰጠዉ አካል ከሆነ ደግሞ ከመቶ ሺ ብር በማያንስና ከሁለት መቶ ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል ፤ የስራ ኃላፊውም ከሦስት አመት በማያንስና ከስድስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም ከሁለት መቶ ሺ ብር በማያንስና ከሦስት መቶ ሺ ብር በማይበልጥ | 3. In the case of a juridical person offence, a person is liable to a fine of not less than one hundred thousand Birr and not more than two hundred thousand Birr, and to a term of imprisonment of the officer in charge of not less than three years and not more than six years, or a fine of not less than two hundred |

| | |
|---|---|
| የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡ | thousand Birr and not more than three hundred thousand Birr or both. |
| ፲፱. ብክለትን በሚመለከት ስለሚፈፀም ጥፋት | 19. Offense relating to pollution |
| ሀ/አንድ የተፈጥሮ ሰው የዚህን አዋጅ ወይም አዋጁን ተከትሎ የሚወጣ ደንብና መመሪያን በመተላለፍ በካይን ወደ አካባቢ በመልቀቅ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ከመቶ ሺ በማያንስና ሦስት መቶ ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአስር አመት በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡ | A/ A natural person commits an offence if he discharges any pollutant contrary to the provisions of this Proclamation or regulations issued following this Proclamation and is liable, on conviction, to a fine of not less than one hundred thousand Birr and not more than three hundred thousand Birr or to an imprisonment of not less than five years and not more than ten years or both. |
| ለ/ጥፋቱን የፈፀመው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ከመቶ ሃምሳ ሺ ብር በማያንስና ከ ሁለት መቶ ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡ የሥራ ኃላፊውም ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአስር ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም መቶ ሺ ብር በማያንስና ከሁለት መቶ ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡ | B/ In the case of a juridical person offence, he/she is liable to a fine of not less than one hundred fifty thousand Birr and not more than two hundred thousand Birr, and an imprisonment of the officer in charge for a term of not less than five years and not more than ten years, or a fine of not less than one hundred thousand Birr and not more than two hundred thousand Birr or both. |
| ፳. ስለመውረስና ወደ ነበረበት ሁኔታ ስለመመለስ | 2. Forfeiture and Restoration |
| በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትሎ የሚወጣ ደንብና መመሪያን በመጣስ ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠበት ማንኛዉም ሰው ላይ ከሚወሰንበት ማንኛውም ቅጣት በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ:- | The court, before which a person is prosecuted for an offence under this Proclamation or regulations and directive issued following this proclamation, may, in addition to any penalty it |

| | |
|---|---|
| ሀ/ለጥፋቱ ተግባር የዋለ ማንኛውም ነገር ተወርሶ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ወይም በሌላ መንገድ እንዲወገድ፤<br>ለ/አካባቢውን የማፅጃ ፣ መሳሪያውን ፣ ኬሚካሉን ወይም ዕቃውን ማስወገጃ ወጪ ተከሳሹ እንዲከፍል ፤ እንደዚሁም<br><br>ሐ/ጉዳት የደረሰበትን አካባቢ ተከሳሹ በራሱ ወጪ ወደ ነበረበት ሁኔታ እንዲመልስ ወይም ደግሞ ይህ የማይቻል ከሆነ ተገቢዉን ካሳ እንዲከፍል ማድረግ፡፡ | impose upon the convicted person, order:<br><br>A/ the confiscation of any thing used in the commission of the offence in favor of the state or to dispose of it in any other way:<br><br>b/ that the cost of cleaning up and the disposing of the substance, chemical or equipment seized be borne by the convicted person; and<br><br>C/ the convicted person to restore to the state in which the environment was prior to the infliction of the damage, and when such restoration is not possible to pay appropriate compensation. |
| **ክፍል አራት**<br><br>**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**<br><br>፳፩. ስለማበረታቻ<br><br>1. ቢሮው ብክለትን ለመከላከል ወይም መጠኑን ለመቀነስ የሚያስችል ማንኛውንም ዘዴ መጠቀም ለሚጀምር ሰው የማበረታቻ ሽልማት ይሰጣል፡፡<br><br>2. ቢሮው ብክለትን ለመከላከል ሲባል ወደ አገር ውስጥ የሚገባ መሳሪያ ከገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ክፊያ ነጻ እንዲሆን ለሚመለከተው አካል | **Part four**<br><br>**Miscellaneous provisions**<br><br>21. Incentives<br><br>1. The Agncey will give an incentive for a person who implements any method that enable the prevention or minimizatin of pollution:<br><br>2. The bureau will write a letter of support to the concerned body for the importation of equipment that is destined to control pollution to be exempted from payment of custom duty. |

| | |
|---|---|
| የድጋፍ ደብዳቤ ይጽፋል፡፡ | |
| ፳፪. የመተባበር ግዴታ | 22. Duty to cooperate |
| ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅና ይህን አዋጅ ተከትለው የሚወጡ ደንቦችና መመሪዎችን ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡ | Any person shall have the duty to cooperate in the implemlentation of this Proclamation and regulations and directives issued following this Proclamation. |
| ፳፫. ስለመሸጋገሪያ ድንጋጌ | 23. Transitory provision |
| በቀድሞ የደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት በወጡ ሕጎች የተሰጡ ዉሳኔዎች ፤ አሰራሮች እና በእንጥልጥል ያሉ ጉዳዮች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ በዚህ አዋጅ እዉቅና አግኝተዉ እንደአስፈላግነቱ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡ | Decisions, procedures, and pending matters based on laws enacted by the former Southern Nations, Nationalities, and Peoples' Regional State Government will remain recognized and, where applicable, continue to be implemented under this proclamation, unless they are inconsistent with this proclamation. |
| ፳፬. መረጃ ስለመስጠት ግዴታ | 24. Duty to provide information |
| 1. የዚህን አዋጅ ወይም ከዚህ አዋጅ ጋር ግኑኙነት ያለውን የሌላ ሕግ ድንጋጌ የሚመለከት ተግባርን የሚያከናውን ማንኛውም ሰው በቢሮው ወይም አግባብ ባለው አካል በሚፈለገው መሠረት የስራ እንቅስቃሴውን መረጃ ማቅረብ አለበት፡፡ | 1. Any person engaged in an activity pertaining to any of the provisions of this proclamation or any other related law shall provide any information on his activity as required by the Bureau or the relevant body. |
| 2. ቢሮው ማንኛውንም ዓይነት አካባቢን የሚመለከት መረጃ የማግኘት መብት አለው፡፡ | 2. The bureau shall have access to all environmental data and information. |

| | |
|---|---|
| ፳፭. ደንብና መመሪያ ስለማውጣት ሥልጣን | 25. Power to issue regulations and directives |
| 1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡ | 1. Council of the regional government may issue regulations for the implement of this proclamation. |
| 2. ቢሮው ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዱ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡ | 2. The bureau may issue detailed guidelines neccessary to implement this proclamation. |
| ፳፮. ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ሕጎች | 26. Inapplicable Laws |
| ከዚህ አዋጅ ጋር ተቃራኒ የሆነ ማንኛውም አዋጅ ፣ ባህል ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡ | Any proclamation, culure or customary practice inconsistent with this proclamation is inapplicable regarding matters provided herein. |
| ፳፯. አዋጁ ስለሚፀናበት ጊዜ | 27. Effective Date |
| ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ከፀደቀበት ታህሳስ 5 ቀን 2016ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡ | This proclamation shall come into force as of the 5th day of December, 2016 E.C. |
| **አርባ ምንጭ**<br>**ታህሳስ 5 ቀን 2016 ዓ.ም**<br>**ጥላሁን ከበደ**<br>**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር** | **Arbaminch**<br>**December15th , 20 23**<br>**TILAHUN KEBEDE**<br>**The Chief Executive of South Ethiopia Regional State** |